የኢትዮጵያ ግብርና
ባለስልጣን
Ethiopian Agricul-
tural Authority

# ዜና ሠፀሐኒት

በሕዝብ ግንኙነትና ኮሙኒኬሽን ስራ አስፈፃሚ በየ3 ወሩ የሚወጣ የውስጥ ጋዜጣ

ቅጽ 1 ቁጥር 75

መስከረም 2019 ዓ.ም

ርዕይ

በዓለምአቀፍ ደረጃ ዕውቅናና ተቀባይነት ያለው የግብርና ተቆጣጣሪ ተቋም ሆኖ ማየት፤

ተልዕኮ

የግብርና ቴክኖሎጂን፣ አገልግሎቶችን፤ ግብዓቶችና ምርቶችን ጥራት፣ ደህንነት፣ ፍቱንነት፣ፈዋሽነት፣ጤናማነትና ቀልጣፋነትን ለማረጋገጥ የሚያስችል፤ መልካም ስም ያለውና፣ለአካባቢ ጥበቃ ተገቢውን ትኩረት የሚሰጥ የቁጥጥር ተቋምና ስርዓት በመገንባትና የግብርና ቁጥጥር ስራዎችን በመተግበር፣ የሀገር ውስጥ እና የአለም ገበያ ተደራሽነትና ተወዳዳሪነትን በማሳደግ ለላቀ ሀገራዊ ጥቅምና የኤኮኖሚ ዕድገት የሚጠበቀትን አስተዋፅኦ ማበርከት

እሴቶች

- ታማኝነት
- ሚስጥር ጠባቂነት
- ቁርጠኝነት
- የህግ የበላይነት
- ተጠያቂነት
- ለደንበኛና ተገልጋይ ትኩረት
- አለማዳላት
- አጋርነት
- ግልጽነት፡፡
- ምላሽ ሰጪነት

አድራሻ፦ ፖ.ሳ.ቁ 31303

ስልክ ቁጥር ፡- 0115534520

የውስጥ መስመር፡- 227/234

ዌብሳይት:- http:www.eaa.gov.et

ፌስቡክ:- Ethiopian Agricultural Authority

ቴሌግራም:-eaapr_1234

## የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን፡ ከዲጂታል ትራንስፎርሜሽን ወደ ላቀ የሬጉላቶሪ አገልግሎት

የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን
Ethiopian Agricultural Authority

የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን በሀገራችን የግብርና ሴክተር ውስጥ ጥራቱን፣ ደህንነቱንና አጠቃላይ ብቃቱን የጠበቀ የቁጥጥር (ሬጉላቶሪ) ስርዓት በመዘርጋት ረገድ ቁልፍ ሚና በመጫወት ላይ የሚገኝ ተቋም ነው። ባለስልጣኑ በአለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ፣ ተቀባይነት ያለውና መልካም ስም ያተረፈ ተቆጣጣሪ ተቋም የመሆን ታላቅ ራዕዩን ለማሳካት ባለፉት ዓመታት አበይት ስራዎችን ሲያከናውን ቆይቷል።

**የ2018 በጀት ዓመት አበይት ስኬቶችና የዲጂታላይዜሽን ጉዞ**

በተጠናቀቀው የ2018 በጀት ዓመት ባለስልጣኑ በዕፅዋትና በእንስሳት የቁጥጥር ዘርፎች ዘመናዊና የተቀናጁ አሰራሮችን በመተግበር በርካታ ውጤታማ ስራዎችን አከናውኗል::

**በዕፅዋት ቁጥጥር ዘርፍ፡** ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡና ወደ ውጭ የሚላኩ የግብርና ምርቶችን ጥራትና ደህንነት ከማረጋገጥ ባሻገር፣ የፀረ-ተባይ፣ የአፈር ማዳበሪያና የዘር ጥራት ቁጥጥር ስራዎችን በከፍተኛ ኃላፊነት በማከናወን የሀገሪቱን የግብርና ምርታማነትና የወጪ ንግድ ተወዳዳሪነት ደግፏል።

**በእንስሳት ቁጥጥር ዘርፍ፡** ለወጪ ገበያ የሚላኩ የስጋና ተረፈ-ስጋ ውጤቶች፣ የቁም እንስሳት የኳራንቲንና የጤና ምርመራዎች፣ እንዲሁም የእንስሳት መድኃኒትና መኖ ጥራትና ፈዋሽነት ፍተሻዎች በጥብቅ ስርዓት እንዲመሩ አድርጓል።

**የዲጂታላይዜሽን ግንባር ቀደምትነት፡**

ባለስልጣኑ አገልግሎቶቹን ሙሉ በሙሉ ዲጂታላይዝ በማድረግ ረገድ በሀገር አቀፍ ደረጃ ግንባር ቀደም ተቋም መሆን ችሏል። የወረቀት አልባ አሰራር፣ የላቦራቶሪ መረጃ አስተዳደር ስርዓት (LIMS)፣ የ ePhyto እና የዘር ትራኪንግ ሲስተሞችን በመዘርጋት የአገልግሎት አሰጣጡን ግልጽ፣ ፈጣንና ከአለም አቀፍ መስፈርቶች ጋር የተጣጣመ እንዲሆን አድርጓል።

## የ2019 በጀት ዓመት ስትራቴጂካዊ የትኩረት አቅጣጫዎች

በ2018 በጀት ዓመት የተመዘገቡትን መልካም ተሞክሮዎችና የዲጂታላይዜሽን ስኬቶች መሠረት በማድረግ፣ ባለስልጣኑ በ2019 በጀት ዓመት ለተገልጋዩ ማህበረሰብ የበለጠ ምቹ፣ ቀልጣፋና ግልፅ የሆኑ አሰራሮችን ለመዘርጋት የሚያስችለውን ስትራቴጂካዊ ዕቅድ አዘጋጅቶ ወደ ሙሉ ትግበራ ገብቷል።

**የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን የ2019 ዕቅድ**

- የዕፅዋት ግብዓትና ምርት ቁጥጥር ዘርፍ
- የእንስሳት ግብዓትና ምርት ቁጥጥር ዘርፍ
- ሜካናይዜሽንና ቴክኖሎጂ ቁጥጥር ዘርፍ

**ተቋማዊ ራዕይና ተልዕኮ**

**ተልዕኮ፡** የግብርና ቴክኖሎጂ፣ ግብዓቶች፣ ምርቶችና አገልግሎቶች ጥራት፣ ደህንነት፣ ፍቱንነትና ጤናማነት ለማረጋገጥ የሚያስችል ብቁ የቁጥጥር ስርዓት በመገንባት፤ የግብርና ምርቶችን የሀገር ውስጥና የአለም ገበያ ተወዳዳሪነት ማሳደግ።

PAGE 3

**ራዕይ፡**

በአለም አቀፍ ደረጃ እውቅናና ተቀባይነት ያለው የግብርና ተቆጣጣሪ ተቋም መሆን፡፡

**የ2019 በጀት ዓመት ዋና ዋና የትኩረት መስኮች**

የዕፅዋት ግብዓቶችና የወጪ/ገቢ ምርቶች ቁጥጥር

በበጀት ዓመቱ የግብርና ምርታማነትን ለማሳደግና ጥራቱን የጠበቀ ምርት ለገበያ ለማቅረብ የተያዙ ዋና ዋና ግቦች፡

የፀረ-ተባይና ማዳበሪያ ቁጥጥር፡ ለ 125,615 ሜትሪክ ቶን ፀረ-ተባይ የፍቱንነትና ጥራት ማረጋገጫ መስጠት፣ ለ 2,551,212 ሜትሪክ ቶን የአፈር ማዳበሪያ ጥራት ምርመራ ማካሄድ እና ለ 255 ድርጅቶች የብቃት ማረጋገጫ መስጠት፡፡

የኳራንቲንና የወጪ ምርት ቁጥጥር፡ ለ 970,000 ሜትሪክ ቶን ወደ ውጭ የሚላኩ የዕፅዋት ውጤቶች የጤንነትና ጥራት ማረጋገጫ በመስጠት የላኪ ሀገራትን ቅሬታ (Notification) መቀነስ፤ እንዲሁም ለ 120,000 ሜትሪክ ቶን ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ ምርቶች የቅድመ-መግቢያ ፍተሻ ማድረግ፡፡

የዘር ጥራትና ዝርያ ጥበቃ፡ 120 ዕጩ የዕፅዋት ዝርያዎችን ገምግሞ 72 አዳዲስ ዝርያዎችን ማስመዝገብና መልቀቅ፣ እንዲሁም 1,150,000 ኩንታል የሀገር ውስጥ ዘር እና 500,000 ኪሎግራም ከውጭ የሚገባ ዘር ጥራት መቆጣጠር፡፡

**የእንስሳት ግብዓቶች፣ ምርቶችና የላቦራቶሪ አገልግሎት**

የእንስሳት ሀብት ልማትን ለማፋጠንና የወጪ ገበያ ተወዳዳሪነትን ለማሳደግ የተነደፉ ስትራቴጂካዊ ግቦች፡

የስጋና ተረፈ ስጋ ኤክስፖርት ፡-27,000 ቶን ስጋና ተረፈ ስጋ ጥራትና ደህንነት አረጋግጦ ለወጪ ገበያ ማቅረብ

የቁም እንስሳት ኤክስፖርት:- 680,000 የቁም እንስሳት የኳራንቲንና የጤና ምርመራ ማካሄድ

የእንስሳት መድኃኒት ቁጥጥር:- 4,000 ቶን የእንስሳት መድኃኒት ደህንነትና ፈዋሽነት ማረጋገጥ

የእንስሳት መኖ ቁጥጥር:- 7,000 ቶን የመኖ ተጨማሪ ንጥረ ነገሮች ማስገቢያ ፈቃድ መስጠትና ጥራት መመርመር

የላቦራቶሪ አገልግሎት:- 10 አዳዲስ አለም አቀፍ እውቅና (Accreditation) ያላቸው የምርመራ አይነቶችን ማደራጀት

የግብርና ምርምር፣ ኤክስቴንሽንና ሜካናይዜሽን ቁጥጥር:- ለ 17 የምርምር፣ ኤክስቴንሽንና ሜካናይዜሽን አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ኢንስፔክሽን ማካሄድ፡፡

ለ 34 ተቋማት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት መስጠት ወይም ማደስ፡፡

ለ 800 ከውጭ የገቡና በሀገር ውስጥ የተመረቱ የግብርና መሳሪያዎች የጥራትና ውጤታማነት ፍተሻ ማድረግ።

**ተቋማዊ ዲጂታላይዜሽንና ዘመናዊ አሰራር**

የቁጥጥር ስራውን ዘመናዊና ቀልጣፋ ለማድረግ ባለስልጣኑ አበይት የዲጂታላይዜሽን ስራዎችን አጠናክሮ እየሰራ ይገኛል፡:

የላቦራቶሪ መረጃ ስርዓት (LIMS) ዝርጋታ፡ የላቦራቶሪ ፍተሻዎችን በሶፍትዌር በማስደገፍ ከ ISO/IEC 17025:2017 መስፈርቶች ጋር ማጣጣም።

ወረቀት አልባ አሰራርና የመሶብ አገልግሎት፡ ePhyto፣ የዘር ሰርቲፊኬሽንና የዘር ትራኪንግ ሲስተሞችን በማጠናቀቅ አገልግሎቶችን ሙሉ በሙሉ ኦቶሜት ማድረግ።

የመረጃ ደህንነትና ክላውድ ማከማቻ፡ የውሂብ ደህንነትን ማረጋገጥና የባክአፕ ስርዓቶችን ሙሉ በሙሉ መዘርጋት።

ባጠቃላይ የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን በ2019 በጀት ዓመት ያቀደው ስትራቴጂካዊ ዕቅድ ተቋሙን በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደገፈ፣ ታማኝና ውጤታማ የሬጉላቶሪ ተቋም አድርጎ ለማስቀጠል ያለመ ነው። የዲጂታል አሰራርን በማጠናከርና የቁጥጥር ስርዓቱን በማሳለጥ ረገድ የተያዙት ግቦች የሀገራችንን የምግብ ዋስትና፣ የዜጎችን ጤናና ደህንነት፣ እንዲሁም የግብርና ምርቶች በዓለም አቀፍ ገበያ ያላቸውን ተወዳዳሪነት በከፍተኛ ደረጃ እንደሚያሳድጉ ይጠበቃል።

## የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን አመራሮች እና ሰራተኞች በአንድ ጀምበር ችግኝ ተከላ አሻራቸውን አኖሩ!!!



የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን በሀገር አቀፍ ደረጃ 800 ሚሊዮን ችግኞችን በአንድ ጀምበር ለመትከል በሁሉም የሀገሪቱ ክፍል ችግኞች ተተክለዋል።

የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን ከግብርና ሚኒስቴር እና ተጠሪ ተቋማት አመራሮችና ሰራተኞች ጋር በጋራ በመሆን በአንድ ጀምበር ችግኝ ተከላ በለሚ ኩራ ክፍለ ከተማ ወረዳ 04 የተለያዩ የከተማ ውበት የዛፍ ችግኞችን በመትከል ሀገራዊ አሻራቸውን አስቀምጠዋል።

## ዘላቂና ውጤታማ የግብርና ቁጥጥር ስርዓትን ለመገንባት የሚያስችል የምክክር ወርክሾፕ ተካሄደ!








የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን በባለስልጣን መስሪያ ቤቶች እና በዋና ዋና ባለድርሻ አካላት መካከል የመረጃ ልውውጥ እና ቅንጅትን ለማጠናከር የሚያስችል ዘላቂነት ያለው የምክክር መድረክ አካሄደ።

በመድረኩ ላይ የክልል ቁጥጥር ባለስልጣናት ተወካዮች፣ የባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ባልደረቦች እንዲሁም በአውሮፓ ህብረት የሚደገፈው የትዊኒንግ (Twinning) ፕሮጀክት ተወካዮች እና ባለሙያዎች ተሳትፈዋል።

በኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን የእፅዋት ኳራንቲን ሪጉላቶሪ መሪ ስራ አስፈፃሚ ወ/ሮ መቅደስ ነጋ ባደረጉት ንግግር፣

የግብርና ዘርፍ ውጤታማና ዘላቂ ሥራ ከአንድ ተቋም ጥረት ብቻ የሚገኝ ባለመሆኑ፣ በተቋማት መካከል ጠንካራ ግንኙነት፣ ፈጣን የመረጃ ልውውጥና ውጤታማ ቅንጅት እንደሚያስፈልግ ገልጸዋል።

የዛሬው ወርክሾፕ ያሉትን የግንኙነትና የቅንጅት ክፍተቶች ለመለየት፣ የተሻለ የመረጃ ልውውጥ ሥርዓት ለመፍጠርና ተግባራዊ የጋራ መፍትሔዎችን ለመወሰን ወሳኝ መድረክ መሆኑንም አመላክተዋል።

በተጨማሪም፣ ተሳታፊዎች ልምዳቸውን፣ ተግዳሮቶቻቸውንና ምክረ ሀሳቦቻቸውን በነፃነት በማካፈል፣ ችግሮችን ብቻ ከመለየት ይልቅ ተግባራዊና ዘላቂ መፍትሔዎችን በጋራ እንዲያዘጋጁ ጥሪ አቅርበዋል።





## የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን ሰራተኞች ደም በመለገስ ሰብአዊ አለኝታነታቸውን አረጋገጡ!!!




የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን አመራሮችና ሰራተኞች «ደም ይለግሱ ህይዎት ያድኑ» በሚል መሪ ቃል በተዘጋጀው የደም ልገሳ መርሃ ግብር ላይ በመሳተፍ ደም በመለገስ አርአያነታቸውን አሳይተዋል። በባለስልጣኑ የሴቶች ጉዳይ ማህበራዊ አካቶ ትግብራ ስራ አስፈፃሚ ወ/ሮ ትግስት ወ/አገኘሁ እንደተናገሩት ሰራተኞች ደም መለገስ የህይወት አዳኝነቱንና አስፈላጊነቱ በመገንዘብ በየዓመቱ የሚያካሂዱትን ይህን መልካም ተግባር ዘንድሮም በተጠናከረ መልኩ የፈፀሙ ሲሆን፣ በርካታ ሰራተኞች በበጎ ፈቃደኝነት ተሳትፈዋል ብለዋል። በመርሃ ግብሩ ላይ የተሳተፉት ሰራተኞች እንደገለፁት፣ ደም መለገስ የሰዎችን ህይወት ከመታደግ ባሻገር የህሊና እርካታን የሚያስገኝ ከፍተኛ ሰብአዊ ተግባር በመሆኑ ይህንን በጎ ተግባር አጠናክረው እንደሚቀጥሉ አረጋግጠዋል።

## የባለሥልጣኑ የዲጂታል አገልግሎት አሰጣጥ ተሞክሮ ለሌሎች ተቋማት አርአያ መሆኑ ተገለጸ።



የኢትዮጵያ ግብርና ባለሥልጣን) -የኢትዮጵያ ህብረት ሥራ ኮሚሽን አመራሮች የኢትዮጵያ ግብርና ባለሥልጣንን የዲጂታል አገልግሎት አሰጣጥና የዲጂታል ሽግግር ተሞክሮ ልምድ ልውውጥ አካሂደዋል። የባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ክቡር አምባሳደር ድሪባ ኩማ፣ ዲጂታል ሽግግሩ የሥራ ሂደቶችን ለማቀላጠፍ፣ የአገልግሎት ፈላጊዎችን ጊዜና ወጪ ለመቀነስ፣ ብልሹ አሠራርን ለማስቀረት፣ ግልጽነትንና

ወደ ገፅ 7 ዞሯል

PAGE 7

ከገፅ 6 የዞረ

የአገልግሎት ጥራትን ለማሳደግ ወሳኝ መሆኑን ገልጸዋል። ባለሥልጣኑ በአሁኑ ወቅት 259 አገልግሎቶችን ዲጂታል ማድረጉን፣ 156 አገልግሎቶችን በኦንላይን እየሰጠ መሆኑን እና 68 አገልግሎቶችን በመሰብ አንድ ማዕከል እየሰጠ መሆኑን አብራርተዋል ።

የውስጥ አገልግሎቶችን ዲጂታል ማድረግ የሥራ ሂደቶችን ከማቀላጠፍ ባለፈ ተቋሙ በዘመናዊ አሠራር እንዲመራ፣ ግልጽነትን እንዲያሳድግና ተወዳዳሪነቱን እንዲያጎለብት እያገዘ መሆኑንም ጠቁመዋል።

ባለሥልጣኑ አገልግሎቶቹን ከወረቀት አሠራር ወደ ዲጂታል ሥርዓት ለማሸጋገር ያጋጠሙ በርካታ ተግዳሮቶችን በመቋቋም ከአጋር አካላት ጋር በቅንጅት በመስራት ለዚህ ውጤት ማብቃት መቻሉን አብራርተዋል ።

የህብረት ሥራ ኮሚሽን ዋና ኮሚሽነር ጌትነት ታደሰ በበኩላቸው፣ ባለሥልጣኑ በአጭር ጊዜ ያከናወነው የዲጂታል ሽግግር ሥራ አበረታችና አርአያነት ያለው መሆኑን ገልጸው፣ ከተሞክሮው ግብዓት እንዳገኙ ገልፀዋል ።

ልምድ ልውውጡ በተቋማቱ መካከል የዲጂታል ልምድ ልውውጥን በማጠናከር፣ በቴክኖሎጂ የተደገፈ አገልግሎትን በማስፋፋት እና ቀልጣፋ፣ ግልጽና ዘመናዊ የመንግሥት አገልግሎትን ለማሳደግ ጠቃሚ ግብዓት መሆኑ ተመላክቷል::

## ከማኑዋል ወደ ዲጂታል፤ ከጊዜና ወጪ ብክነት ወደ ቀልጣፋ፣ ግልጽና ተጠያቂ አገልግሎት!

የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን የዲጂታል ኢትዮጵያ 2030 ስትራቴጂን በመተግበር ላይ ሲሆን፣ አገልግሎቶቹን በዲጂታል መድረኮች ማለትም እንደ eService እና Single Window እንዲሁም በራሱ ባለማቸው ኦንላይን ፕላትፎርሞች በማቅረብ የዜጎችን እና የንግድ ተቋማትን አገልግሎት ለማሻሻል ጥረት በማድረግ ላይ ይገኛል ።

ባለሥልጣኑ በአጠቃላይ 462 የተለዩ አገልግሎቶች ካሉት ውስጥ 259 አገልግሎቶችን ዲጂታል አድርጓል። ከእነዚህም 130 በeService እና 26 በESW፣ በአጠቃላይ 156 አገልግሎቶች በቀጥታ ኦንላይን እየተሰጡ ሲሆን፣ 68 አገልግሎቶች ወደ መሶብ ማዕከል ገብተዋል። 19 አገልግሎቶችን ወደ ዩኒፋይድ መሶብ ለማስገባት ተለይተዋል ፡ ፡

ይህ ሽግግር ተገልጋዮች ከማንኛውም ቦታ ሆነው በኢንተርኔት ማመልከት፣ የአገልግሎታቸውን ሂደት መከታተል እና የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት ማግኘት እንዲችሉ አስችሏል ።

በተጨማሪም የዲጂታል አሰራሩ የአመልካቾችን አካላዊ ተገኝቶ መገልገልና የወረቀት ወጪን በመቀነስ ጊዜና ወጪ ለመቆጠብ አስችሏል፤ እያንዳንዱ የማመልከቻ ደረጃ በሲስተሙ መመዝገቡም ግልጽነትና ተጠያቂነትን አጠናክሯል ።

ከዚህ ባለፈ፣ የኢ-ፋይቶ (e-Phyto) ስርዓት ከዓለም አቀፉ IPPC Hub ጋር በመቀናጀቱ ባለሥልጣኑ ከ186 አገሮች ጋር የኤሌክትሮኒክ ፋይቶሳኒተሪ ሰርተፍኬት ልውውጥ ማድረግ ችሏል።

## የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን በሸገር ከተማ ለሚገኙ ተማሪዎች የትምህርት ቁሳቁስ ድጋፍ አደረገ!!!



የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን በሸገር ከተማ አስተዳደር ኤካ ጣፎ ክፍለ ከተማ፣ ደንበል ጣፎ ወረዳ፣ ወበሪ ቁጥር 1 ቡኡራ በሩ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ለሚማሩ ተማሪዎች የማስጀመሪያ የትምህርት ቁሳቁስ ድጋፍ አድርጓል። ይህ ድጋፍ በተለይም ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው ወላጆችና ተማሪዎች አዲሱን የትምህርት ዘመን ያለ ስጋት እንዲጀምሩና በትምህርታቸው ላይ ብቻ ትኩረት እንዲያደርጉ ለማስቻል ታስቦ የተዘጋጀ መሆኑ ተገልጿል። በስነ-ስርዓቱ ላይ የባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ጽ/ቤት ሀላፊ አቶ መሰሉ ዋጋው እንደገለጹት፤ ግብርናን ማዘመን የሚቻለው በትምህርት የበለጸገ ትውልድ ሲፈጠር በመሆኑ፣ ተቋሙ ከሙያዊ ስራው ጎን ለጎን የነገ ሀገር ተረካቢ ህጻናትን መደገፉን አጠናክሮ ይቀጥላል ብለዋል። የትምህርት ቤቱ አስተዳደር ወ/ሮ ነጢ ኢቲቻ በበኩላቸው የተደረገውን በጎ አድራጎት አድንቀው፣ ለተደረገው ድጋፍ ሙሉ ምስጋናቸውን አቅርበዋል።

## ባለስልጣኑ ጳጉሜን 4 የኅብር ቀንን በድምቀት አከበረ!!

የኢትዮጵያ ግብርና ባለሥልጣን ጳጉሜን 4 ታስቦ የዋለውን የኅብር ቀን አመራሩና ሠራተኞቹ በተገኙበት በድምቀት አከበረ። ባለስልጣኑ ብዝኃነትን እንደ ጸጋና የጋራ ዐቅም በመጠቀም፣ የተመዘገቡ ተቋማዊ ስኬቶችን በማጽናት የግብርናውን ዘርፍ ዘመናዊ፣ ተወዳዳሪና ውጤታማ ለማድረግ የሚያስችሉ ሥራዎችን አጠናክሮ መቀጠል እንዳለበት በመድረኩ ተመላክቷል። የባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ክቡር አምባሳደር ድሪባ ኩማ በመክፈቻ ንግግራቸው፤ የኅብር ቀን ዋና ዓላማ የተለያዩ ማንነቶችን በማክበር የጋራ ሀገራዊ እሴቶችን ማጠናከር መሆኑን ገልጸው፣ ተቋሙ የኢትዮጵያን ሁለንተናዊ ጥቅም ከሚያረጋግጡ ቁልፍ ተቋማት መካከል አንዱ መሆኑንም ጠቁመዋል። ባለሥልጣኑ በወጪና ገቢ የግብርና ምርቶች ላይ ጥራትና ደህንነትን በማረጋገጥ ለሀገራዊ ኢኮኖሚ ዕድገት ምቹ ሁኔታዎችን ከመፍጠር ባሻገር፣ የዲጂታል ሽግግር ሥራዎችን አጠናክሮ መቀጠሉን ዋና ዳይሬክተሩ አብራርተዋል። በዚህም መሠረት ከሚሰጣቸው 462 አጠቃላይ አገልግሎቶች ውስጥ 259 አገልግሎቶች ወደ ዲጂታል ሥርዓት መሸጋገራቸውን ገልጸው፤ ከእነዚህም 156 አገልግሎቶች በቀጥታ ኦንላይን እየተሰጡ መሆናቸውንና 68 አገልግሎቶችን ወደ መሶብ ማዕከል በማስገባት አገልግሎት እየተሰጠ መሆኑን በመግለጽ ሌሎች አገልግሎቶችን ዲጂታል ለማድረግ ስራዎች እየተሰሩ መሆኑን አስገንዝበዋል፡፡

በመጨረሻም የኢትዮጵያ ግብርና ባለሥልጣን የእጽዋት ሬጉላቶሪ ዘርፍ ም/ዋና ዳይሬክተር ወንዳለ ሀብታሙ (ዶ/ር) ባስተላለፉት መልዕክት፣ የተመዘገቡ ስኬቶችን በማጽናትና በትብብር አሠራር ላይ በመመሥረት የግብርናውን ዘርፍ የበለጠ ተወዳዳሪ ለማድረግ የሚደረገው ጥረት ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ገልጸው፤ ሁሉም ሠራተኛ ብዝኃነትን በማክበር በሀገር ግንባታ ዙሪያ ትኩረት አድርጎ መሥራት እንዳለበት አሳስበዋል።

## አዝናኝና አስተማሪ ቀልዶች







## የታላላቅ ሰዎች አባባል




